# <u>እኔም የምለው አለኝ!</u>

<u>ከወንደወሰን ዘገዬ</u>

እኔም ስለ አብርሃ በላይ የምለው ነገር ቢኖረኝ የዶክተር ታደሰ ቡላ ዓርአያነትን ተከተለኩ። ስለ ደብተራው ድረ ገጽ አዘውትረን ተከታታይ መሆናችንን የሚገልጽ ደብዳቤ ከዚህ ቀደም (ከጓደኞቼ ጋር አንዳንድ ተያያዥና የወደድናቸውን አርቲክሎች አያይዘን) በኢሜላችሁ መላካችንን አስታውሳለሁ። እኔ ብቻ አይደለሁም ሌሎች አብረውኝ የሚኖሩ ጓደኞቼም ጭምር እንጂ። እንደ ታደሰ ቡላ ሁሉ እኔም ድረ ገጾችን ስጎበኝ የአብርሃ በላይን ዌብ ሳይትም አልፎ አልፎ አብሬ እጎበኝ ነበር። በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ አያልነሽ የፕሮፌሰር ይስሐቅ ኤፍሬምን ''የሽምግልና'' ሂደት ተችታ የጻፈችውን ጽሁፍ ተመልከቼ በጽሁፉ አነሳሽነት ውይይት ተከፍቶ ስነጋገር እጅግ የተቆጡትና የተበሳጩት ጥቂት የኢትዮ ሚዲያ እድምተኞች ነበሩ። እኔም ምክንያቱ ስላልገባኝ ተደናግሬ በነገሩ ላይ ብዙ ከማለት ተቆጠብኩ። እንዲያም ሆኖ ግን ኢትዮ ሚዲያን መጎብኘቴን አላቆምኩም። በኋላ በኋላ ላይ ለመፈተን ወደ ኢትዮ ሚዲያ አንድ ሁለት ጽሑፍ ሰደድኩ ሁለቱንም ሳያወጡት ቀሩ። ቆይቼ ሰዬ አብርሃ በተፈታ ስሞን ጠብቄ፣ አሁንም ሌላ ጽሁፍ መፍታቱን አብስሬ ጻፍኩ፤ ወዲያውኑ አወጡት። ከዚህ በኋላ የኢትዮ ሚድያን አካሄድ በጥሞና የምከታተል ሰው ሆንኩ።

በነገራችን ላይ የአያልነሽን ጽሑፍ የምከታተል ሰው ነኝ። ይህንን የአያልነሽን ጽሁፍ ያልወደዱት የኢትዮ ሚዲያ እድምተኞች በሙሉ፣ ቀደም ሲል የወያኔ አባሎች የነበሩ፣ አሁንም ደግሞ በዓለም ላይ ተብተነው በየፖለቲካው መድረክ አለን አለን የሚሉ ግለሰቦች ናቸው። እነርሱ ለመሆናቸው መረጃው አለኝ። "በጎ ነገር የሚሰራን ሰው የማይወዱ'' በማለት ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅን የተቸችበትን ጽሁፍ ያለወደዱት የአብርሃም በላይ የቅርብ ወድጆችና የወያኔ አገልጋይ የነበሩ ጥቂት ግለሰቦች እውነት ለመናገር ለፕሮፌሰሩ አስበው ሳይሆን፣ ፕሮፌሰሩ ሊያድኑት የሚሞክሩትን የወያኔን ስርዓት ለመታደግ ነው። በእነ አብርሃ በላይ አሰተሳሰብ ከወያኔ ውስጥ መለስን አግልሎ፣ ወያኔንን እንደ ሥርዓት ማቆም የሚመኙት ህልማቸውና ሌት ተቀን የሚሰሩለት ተግባራቸው እንደሆነ ስለማውቅ ነው። ልብ በሉ ትዝ ይላችሁ እንደሆነ ያኔ የቅንጅት መሪዎች ታስረው የነበረበትና በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊም የታሰሩት እንዲፈቱ፣ ወያኔ የሰረቀውን የሕዝብ ድምፅ እንዲመልስ የሚያጋልጥ ሰላማዊ ሰልፍ በተከታታይ ይደረግ የነበረበት ወቅት ነው። በዚህ መኃል የታሠሩትን የቅንጅት መሪዎች ለማስፍታት በፕሮፌሰር ይስኃቅ መሪነት ከመንግሥት ጋር ''ሽምግልና" እንደተያዘና ድርድር እየተደረገ እንደሆነ ወሬ ይሰማል። ይህ በዚህ እንዳለ ፕሮፌሰር ይስኃቅን የሚተች ጽሁፍ በአያልነሽ በኩል ብቅ ይላል። የጽሁፉ ይዘት HR 2003ን መቃወማቸውን አንተርሳ አቋማቸውን የሚፈትሽ ጽሁፍ ነበር። በወቅቱ ብዙዎቻችንም ፕሮፌሰሩ HR 2003ን መቃወማቸው ያስገረመን ጉዳይ ነበር። በእነ አብርሃ በላይ ታዳሚዎች አማካኝነት ''በጎ ሥራ'' የሚሰሩ ተብለው እንዳይነኩ የተባሉት ፕሮፌሰር ኤፍሬም፣ ዛሬ ሚናቸው ምን እንደሆነ እያየነውና በአደባባይ እየታዬ ነው። እንዲህ ዓይነት የተበላሸ መንገድን የሚከተሉና ህዝብን የሚያውናብዱ ግለሰቦችን ቀድመው በመመልከት የሚያስከትሉትን ችግር ቀድመው በማጋለጥ የሚጽፉ ሰዎችን እንዲሁ ከመሬት ተነስተን ላለማደመጥ የምናደርገው ሂደት ምን ያህል እንደጎደን ዛሬም የተረዳን አይመስልም። በኢትዮ ሚዲያ ታዳሚዎች በክብረ ነክ የታየው የአያልነሽ ጽሁፍ ይሄ ነበር፥ የጽሁፉ ርእስ "ፍኖተ ሠላም፣ ፍኖተ ዕርቅ" በሚለው ስር ያስቀመጠችው እንደነብርም አስታውሳለሁ

*"ክቡር ፕሮፌሰር! ፍኖተ ሠላም፣ ፍኖተ ዕርቅ ጎዳናው እጅግ ውስብስብ ነው።*
*ፕሮፌሰር እንዳሉት ቀላል አይደለም፤ ፕሮፌሰር እንደሚሉትም ''ሠላም''*

*አለ፤ የሌለው "ፍቅር" ነው ይሉና ሠላሙ በኢትዮጵያ መትረፍረፉን ሲገልጹ ተኩሰ የለም ሰውም እንደልቡ ወጥቶ ይገባል፣ ይልቅሰ የሌለውና የጎደለው "ፍቅርና እርቅ" ነው፣ አብሮ ቡና መጠጣት መሳሳም ግን የለም ብለው ስለ "ሠላምና ዕርቅ" ያላቸውን ምሁራዊ ግንዛቤ አስረድተዋል። በእኔዋ ሚጢጢ እውቀት ደግሞ "ሠላም" ካለ ጠብ የለም፤ ጠብ ከሌለ ደግሞ እርቅ የሚባል ነገር አይነሳም ወዘተ...." ሙሉን ፍኖተ ሠላም ፍኖት እርቅ የሚለውን የአያልነሽን ፅሁፍ ተመልከቱ*

ይሄን ነበር ያለችው። ታዲያ ይሄ ምኑ ነው ክብረ ነክ የሚሆነው፣ እንዲያውም ፕሮፌሰሩ የሚሄዱበትን መንገድ ነው የተቸችው። ይሄ ደግሞ መለመድ ያለበት ጥሩ ባህል ነው ብዬ አምናለሁ- ዴሞክራሲን ለማምጣት የምንፈልግ ከሆነ ትችቶች አስተያየቶች ሰበዕናን እስካልነኩ ድረስ ጠቀሜታቸው አንድና ሁለት አይባልም። ዴሞክራሲን ለመግንባትም ሆነ በበጎ መንገድ ለመጓዝ ከተፈለገ መንገዱ ይሄ ነው። ዛሬም እኮ ከ"ሽምግልናው" በኋላም ወያኔ በብርቱካን ሚድቅሳና በቴዲ አፍሮ ላይ የፈፀመውን ድርጊት እያየን ነው። እንዲያውም እነ ብርቱካንን ለማስፈታት "ሽማግሌ" የነበሩት ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ዛሬ በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል። ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያኖች የምንሳሳተው በሚጻፉና ውይይት የሚጋብዙ ትችቶች ሲቀርቡ፣ በነገሮቹ ይዘት ላይ ማተኮሩን ተተን በጸሃፊዎቹ ላይ እናነጣጥርና ልናልፋቸው የማይገቡ ቁም ነገሮችን እንደ ቀልድ እንዘላቸዋለን። እንዲህ ዓይነት ባህሪን ደግሞ የተላበሱትና ያወረሱን ወያኔ/ኢህአዴጎች ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ በወያኔ/ኢሕአዴግ አማካኝነት የሚሠራው ግፍ ለእነ አብርሃም በላይ ጎልቶ አይታያቸውም። ለማየት ከሞከሩም ያው በተሸዋረረው የዘረኝነትና የጠባብነት መነፀራቸው፣ በአፍቃሪ ወያኔነት እይታቸው ነው።

አብርሃ በላይ በጣም ስር የሰደደ የጠባብነት በሽታ እንዳለውና "የትግራይ ትግርኝ" (የነስዬው ማንፌስቶ) በእነ ስዬ በኩል ቢፍጸምለት የሚወድ እንጅ የሚጠላ አይደለም። አሁንም በዌብ ሳይቱ የሚያስተናግዳቸው አብዛኛዎቹ ማለት ይቻላል ወያኔን የመሠረቱ አሊያም ወያኔን እዚህ ያደረሱ ግለሰቦችን ነው። የአብርሃ በላይ ዓላማው ወያኔን በእነ ስዬና በመሰሎቹ እንድገና መመለስና ለማንገስ ነው። ኢትዮጵያ የሚለውን ስም የሚጠቀመው ለሽፋን ነው፣ ከልቡ ከሆነም ከ"ትግራይ ትግሪኝ" በታች አስቀምጦ ነው።

ኢትዮ ሚዲያን በተመለከተ አሁን ታደሰ ቡላ የደረሱበት መደምደሚያ እኔም ጋ ደርሶና አጋጥሞኝ አይቸዋለሁና ዶክተር ታደሰ ቡላ ደፍረው ይህንን በማውጣትዎ በዚህ አጋጣሚ እያመሰገንኩ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሜ እኔም አንዳንድ እኔን መሰል/ለመሰሉ የዋሆች፣ ኢትዮ ሚዲያ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቅ መስሏቸው የተጃጃሉ ካሉ ነቃ እንዲሉ ነው። አሁንም ስለ እውነት እላችኋለሁ የአብርሃም በላይ ድረ ገጽ (ኢትዮ ሚዲያ) አግልግሎት የሚሰጠው ለወያኔና በወያኔ ዓይነት የዘርና የጠባብነት በሽታ የተለከፉ ህሙማን መነሃሪያ ነው። በአጭሩ ድረ ገጹ የወያኔ ፎቶ ኮፒ የሆኑ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና መሪ ነን ባዮች የሚስተናግዱበት ነው። ነገር ግን ሁሉም ሽፋናቸው መከረኛዋ ኢትዮጵያ ናት። የአብርሃ በላይ ዌብ ሳይትስ መጠሪያው ኢትዮ ሚዲያ አይደል የሚለው!

ደብተራዎች! በምታበረክቱት ሥራ የምንኮራባችሁ ነን። ይህንን መሰል ተግባራችሁን ደግሞ በዚሁ መንገድ እንድትቀጥሉበት አደራ እንላለን። ዘወትር ድረ ገጻችሁን በቁርስ፣ በምሳና በራት ሰዓት እንደ ስኒማ ሳንጎበኛችሁ አናልፍም። እንዲሁም ኢትዮ ላዮንም ከምንመርጣቸው ደረ ገጾች አንዱ ነው። በነገራችን ላይ ወያኔ/ኢሕዴግና

ጠ/ሚኒስቴራችን መለስ ዜናዊ በዋናነት በማንኛውም ጊዜና ሰዓት የሚከታተሉት ዌብ ሳይት ደብተራውን እንደሆነ ታውቃላችሁ? በርቱ ደብተራዎች!

ወንደወሰን ዘገዬ
ሕንድ (ቦንቤ)
February 13/ 2009